የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡» 2ጢሞ. 3÷16-17




«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል፡፡»
መዝ. 118(119)÷130

**Global Good News Literature**
**የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት**
**P.O.BOX 451336**
**Los Angeles, CA 90045**
email: info@globalgoodnews.org
**Copyright © 2008**



## ማውጫ

ክፍል ፭

ገጽ
ትምህርት አምስት ፦ የአማኞች ኅብረት........................................ 5
የአማኞች ኅብረት ምንድን ነው? ......................................... 5
የክርስተያን ኅብረት ........................................................... 6
የኅብረት አስፈላጊነት ........................................................ 6
አማኞች በኅብረት ሲኖሩ የሚከናወኑት ነገሮች ..................... 6
ኅብረትን ማጠናከሪያ መንገዶች .......................................... 7
አስፈላጊ ጥንቃቄ ............................................................... 8
ኅብረት ከሚሻክርበት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ፡- .................. 9
ትምህርት አምስት፡- የአማኞች ኅብረት - ጥያቄዎች ........................ 11

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው፡፡ «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን፡፡

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል፡፡ ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል፡፡ ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ፡፡

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል፡፡ አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው፡፡ ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን፡፡

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን፡፡





# ክፍል ፩




**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል፡፡»
መዝ. 118(119)፥130**

## ትምህርት ዐምስት፡-
## የአማኞች ኅብረት

### የአማኞች ኅብረት ምንድን ነው?

በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሚሰጠውን የዘላለም ሕይወት ያገኙ ሰዎችን ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ «...የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ጴጥ. 2፥9) ይላቸዋል። ይህም ማለት በክርስቶስ ያመነ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ወገን ሆኗል ማለት ነው። ስለዚህም አንዱ አማኝ ለሌላው አማኝ ወገን ነው። አማኝ ሁሉ ከአንዱ ከእግዚአብሔር መንፈስ ስለሚጠጣ አንድነት አለው (1ቆሮ. 12፥12-13)። ሐዋርያው ዮሐንስ፣ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።» ይላል (ዮሐ. 1፥12)። እንደገናም ሐዋርያው አንደኛውን መልእክቱን የጻፈበትን ምክንያት ሲገልጽ፣ «እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።» ይላል (1ዮሐ. 1፥3)። እነኚህንና የመሳሰሉትን ጥቅሶች ስንመለከት፣ እያንዳንዱ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ስላለውና የእግዚአብሔር ልጅ ስለ ሆነ፣ የሌላው ወንድም ወይም እኅት መሆኑ ግልጽ ነው። የአንዱ የክርስቶስ አካል ክፍል ሆኖአልና።

የአማኝ የእርስ በርስ ዝምድና ወይም ኅብረት በአመኑ ጊዜ የተመሠረተ ይሁን እንጂ ይህንን ኅብረት ማሳደግና በሚታይ መንገድ መግለጽ አስፈላጊ ነው። በመዝሙር 133፥1-3፣

«ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፣

እነሆ፣ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው።

ከራስ እስከ ጢም እንደሚፈስስ፣

እስከ አሮን ጢም፣

በልብሱ መደረቢያም እንደሚወርድ ሽቱ ነው።

በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ አርሞንኤም ጠል ነው፤ በዚያ

እግዚአብሔር በረከቱን፣ ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና።»

የሚለው ቃል የሚያመለክተው የክርስቲያኖች ኅብረት ለሌሎች የሚታወቅ መልካም መዐዛና ውበት ያለው፣ የሚያረካና የማያቋርጥም መሆኑን ነው። አማኞች በመግባባትና በአንድነት ሲኖሩና ሲመላለሱ፣ ውበትና መልካም መዐዛ እንዲኖረው ምክንያት የሚሆነው የእግዚአብሔር በረከትና ሕይወት ያለማቋረጥ ይፈስሳል። ይህም ስለ ሆነ ነው በሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ኅብረትን በማድረግ ትጋትን ያሳዩ የነበረው። እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ «ቃሉንም የተቀበሉ... በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራንም በመቍረስ





በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። ... በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፣ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።» (ሐዋ. 2፥41-47)፤ «ተፈትተውም ወደ ወገኖቻቸው መጡና የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ያሉአቸውን ሁሉ ነገሩአቸው። እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ፤ ... ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ። ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው።...» (ሐዋ. 4፥23፡24፡31፡32)

### የክርስተያን ኅብረት

እውነተኛ ክርስቲያናዊ ኅብረት ከሰብኣዊ ድርጅት ኅብረት በአመራሩና በዐላማው ይለያል።

1. *መንፈሳዊ ነው፤ ስለሆነም መለኮታዊ መመሪያን ይከተላል፤ መመሪያውም የእግዚአብሔር ቃል ነው።*

2. አንድ ልብ፣ አንድ ሐሳብንና አንድ መንፈስን ይጠይቃል፤ ይህም አንድነት የሚመጣው እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን ዐላማ ሲያውቅና ስለ መንፈሳዊ ኅብረትም ጥሩ መረዳት ሲኖረው ነው።

### የኅብረት አስፈላጊነት

«ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፣ መሰብሰባችንን አንተው። እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።» (ዕብ. 10፥24-25)

በክርስቶስ በማመን የተገኘው ዝምድና ዐብሮ በመገናኘት ይዳብራል፤ ፍሬውም ይገለጻል።

### አማኞች በኅብረት ሲኖሩ የሚከናወኑት ነገሮች

1. ፍቅር ያድጋል፤ የሚገለጥ መንፈሳዊ ፍሬም ነው። ፍቅር ይገለጥ ዘንድ ከገላጩ ሌላ ተቀባይ ሰው መኖሩ አስፈላጊ ነው። ብቻውን የሚኖር ሰው ሰውን እንደሚወድ ቢናገር እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው። ፍቅር በመተያየት፣ ዐብሮ በመጸለይ፣ በየጊዜው እየተገናኙ በመመካከር፣ ሐዘንንና ደስታን በመከፋፈል ያድጋል። ምንም እንኳ አማኝ ሁሉ ፍቅርን ከእግዚአብሔር የወረሰ ቢሆንም፣ ይህ የወረሰው ባሕርይ በትክክል እንዲያድግ የመትጋት ኀላፊነት አለበት።

2. ለበጎ ሥራ ያነቃቃል፤ ለአንድ ዐላማ የተሰለፉና በየጊዜው እየተገናኙ የሚመካከሩ ሰዎች በዐጭር ጊዜ በጣም የከበረ ብዙ ነገርን መሥራት ይችላሉ:: ይልቁንም በጌታ የሆኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ብርቱዎች ይሆናሉ::
3. ለመመካከርና የጠራ ሐሳብ ለመያዝ ይቻላል:: የእግዚአብሔር ሥራ ጥራት ባለውና በተቀነባበረ መንገድ የሚሠራው የእግዚአብሔር ሰዎች እየተገናኙ ሲጸልዩና ሲመካከሩ ነው::

4. ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለማቋረጥ እንዲፈስስ የታዘዘውን ሕይወትና በረከት መቀበል ይኖራል::

5. እያንዳንዱ አማኝም ሆነ በአጠቃላይ ኅብረቱ ያድጋል:: አማኞች መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ ያደላደለው የተለያየ የጸጋ ስጦታ አላቸው:: ይህም ስጦታ አገልግሎት ላይ የሚውለው አካሉን (አማኞችን) ለማነጽና ለማሳደግ ነው:: ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ኅብረት ሲኖራቸውና ሲገናኙ፣ በጸጋ ስጦታ አንዱ ሌላውን ስለሚያገለግል መንፈሳዊ እድገታቸው ይፋጠናል::

6. አካሉ በሙላትና በትክክል ይሠራል፤ ከላይ እንደ ተጠቀሰው በኅብረት ውስጥ እግዚአብሔር የሰጠው የአገልግሎት ስጦታ ሁሉ (1ቆሮ 12÷4-11፤ ሮሜ 12÷4-8፤ ኤፌ. 4÷7-12) እንደሚገባ ከሠራ አካሉ በትክክል ይሠራል:: ማለትም እግዚአብሔር ያቀደው ነገር ሁሉ ይከናወናል:: ስለዚህ አማኝ ሁሉ በተሰጠው ጸጋ አካሉን ለመገንባት መትጋት አለበት::

<u>ኅብረትን ማጠናከሪያ መንገዶች</u>

የክርስቲያን ኅብረት ሰው የሚፈጥረው ሳይሆን፣ በጌታ በማመን የሚገኝ መለኮታዊ ክንዋኔ ነው:: ይህም ክንዋኔ የሚያድገውና የሚጠናከረው መለኮታዊ መመሪያን ተከትሎ ሲፈጸም ነው:: አንድነት የሚጠበቀው ከዚህ በታች (በኤፌ. 4÷2-3፤ በፊል. 2÷1-5፤ ጥቅሶቹን በሙሉ ያንብቡ) በተዘረዘረው መሠረት:-

- በትሕትና፣
- ሌላውን ከራስ ይልቅ የሚሻል አድርጎ በመቊጠር፣
- ከወገናዊነት በመውጣት፣
- የራስን ጥቅምና ክብር ባለመፈለግ፣
- በየውሃት፣ በትእግሥት፣ በፍቅርና፣ በሰላም ነው::

በገላትያ 5÷22-23 የተዘረዘሩት የመንፈስ ፍሬዎች ማለት ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትእግሥት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት፣ በሕይወታችን ሥር እየሰደዱ በሄዱ ቊጥር የመንፈስ አንድነታችንም እያደገና እየጠነከረ ይመጣል:: እነኚህ ፍሬዎች በሕይወታችን እንዲታዩ





ደግሞ በመንፈስ መመላለስ አስፈላጊ ነው:: የሥጋን ምኞት ለመፈጸም መሯሯጥ ካለ፣ መነካከስና መበላላትም እየጨመረ ይሄዳል:: ስለ መንፈስ ማሰብ ሲያድግ ደግሞ ዕርቅና ሰላም ይበዛል:: «በመንፈስ ብንኖር፣ በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ:: እርስ በርሳችን እየተነሣሣን እየተቀናናን በከንቱ አንመካ::» (ገላ. 5÷25-26)

<u>አስፈላጊ ጥንቃቄ</u>

የአማኞች ኅብረት እግዚአብሔር ከልጆቹ የሚፈልገው ነገር ነው:: በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17፣ ጌታ ኢየሱስ አጠንክሮና ደጋግሞ የጸለየበት ርእስ፣ ደቀ መዛሙርቱና በእነርሱ ምስክርነት ጌታን የሚያውቁ ሁሉ አንድ ይሆኑ ዘንድ ነው:: «ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን <u>እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ</u> በስምህ ጠብቃቸው» (ቊ 11)፤ «<u>ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ</u> ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ አንተ አባት ሆይ፣ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ <u>በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ</u> እለምናለሁ:: እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፣ <u>በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ</u> የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ::...» (ቊ. 20-23)

<u>ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ አማኞች ኅብረት የምንረዳው:-</u>

1. እግዚአብሔርን ከምንመስልበት ነገር አንደኛው መንገድ እንደ ሆነ፣

2. ክርስቶስ በእግዚአብሔር ወደ ዓለም የመላኩ ማረጋገጫ እንደ ሆነ፣

3. በአብና በክርስቶስ የመሆን ምልክት እንደ ሆነ፣

4. ከአብና ከወልድ ጋር መተባበር እንደ ሆነ፣

5. በእግዚአብሔር የመወደዳችን ምልክት እንደ ሆነ ነው::

ስለሆነም በኅብረት መኖር በጣም የከበረና አማኞች ሁሉ ከፍተኛ ዋጋና ጥንቃቄ ሊሰጡት የሚገባ ጉዳይ ነው:: የክርስቲያን ኅብረት ሁልጊዜ አመቺና ቀላል በሆነ መንገድ ይከናወናል ማለት አይቻልም:: የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸመውና ባርኮቱም ወደ ሕዝቡ በሙላት የሚመጣው፣ ቅዱሳኑ በኅብረት በሚኖሩበት ጊዜ ስለ ሆነ፣ ጠላት ኅብረትን አጥብቆ ይዋጋዋል:: ስለዚህም ዐልፎ ዐልፎ በኅብረቱ መካከል ችግሮች ይነሣሉ:: የአንድ ብልት ችግር ላይ መውደቅ በአካሉ ውስጥ ያሉትን ብልቶች ሁሉ ይነካል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ከዚያ ችግር ለመሸሽ ከኅብረቱ ከመውጣት ይልቅ፣ ኅብረቱ ፍጹም መልኩን እንዲይዝ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እየተመካከሩ መፍትሔውን በጸሎት መፈለግ ተገቢ ነው:: ጠላት በኅብረት ውስጥ ቀዳዳ ካገኘ፣ በወገኖች መካከል

መራራቅ እየፈጠረ እስከ መለያየት ያደርሳል፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «ለዲያብሎስ ፈንታ አትስጡ» (ኤፌ. 4÷27) የሚለው፡፡

__ኅብረት ከሚሻክርበት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ፡-__

ሀ. ኀጢአት ሲኖር፡- ኀጢአት ሰው ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር የመለያየት ባሕርይ አለው፡፡ የመጀመሪያው ሰው አዳም ኀጢአትን ባደረገ ጊዜ በመንፈስ ሞተ፤ ከአምላኩም ተለየ፤ ስለ አደረገው ነገር በተጠየቀም ጊዜ ሚስቱን ሔዋንን ከሰሰ (ዘፍ. 3÷10-11)፡፡ በኅብረት ውስጥም እንደዚሁ ኀጢአት ሲገባ መንፈስ ቅዱስን ስለሚያሳዝን፣ በአማኞች መካከል የመንፈስ ውሕደት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

ለ. መከባበር ሲጐድል፡- በመሠረቱ መከባበር የሚጐድለው ራስን ከፍ በማድረግና የክርስቲያንን ማንነት በቅጡ ማወቅ በማይኖርበት ጊዜ ነው፡፡ አንድ ጊዜ የጌታ ደቀ መዛሙርት እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያሉ እርስ በርስ ይከራከሩ ነበር፡፡ ጌታም፣ «ከመካከላችሁ ከሁሉ መብለጥ የሚፈልግ ቢኖር፣ ከሁሉ አነስተኛ በመሆን ሁሉንም ያገልግል» አለ (ማር. 9÷36)፡፡ ከዚያም አንድ ሕፃን ጠርቶ በመካከላቸው በማቆም፣ «እንደዚህ ያለውን ሕፃን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን አባቴን ይቀበላል፤» አለ (ማር. 9÷37)፡፡ አንዱ አማኝ ከሌላው አማኝ እንደሚበልጥ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የሚሞክር ከሆነ፣ ኅብረቱ ክርክር የበዛበት ኅብረት ይሆናል፡፡ አማኝ ሁሉ ማሰብ ያለበት አንድ አማኝ ማንም ይሁን ማን፣ በክርስቶስ ተቀባይነትን ከማግኘቱ የተነሣ የከበረ ስለ ሆነ፣ መከበር እንዳለበት ነው፡፡

ሐ. የራስን ጥቅም ብቻ መፈለግ ሲኖር፡- አንድ ጊዜ የዘብዴዎስ ልጆች ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ «መምህር ሆይ፣ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንወዳለን አሉት፡፡ እርሱም ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ እነርሱም በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝ አንዳችንም በግራህ መቀመጥን ስጠን አሉ፡፡» (ማር. 10÷35-37) ይህ ጥያቄ የበላይ ለመሆን መውደድንና የራስን ጥቅም ብቻ መፈለግን የሚያሳይ ስለ ሆነ፣ የቀሩት ዐሥሩ ደቀ መዛሙርት በሰሙ ጊዜ ያዕቆብንና ዮሐንስን ይቈጡ ጀመረ (ማር. 10÷41)፡፡ የሁለቱ ወንድማማች ጥያቄ ጌታ ሲጠ ራቸው በእነርሱ ሊያደርግ የወደደውን እንዲፈጽም በመዘጋጀት ፈንታ፣ የራሳቸውን ፈቃድና ጥቅም በመውደዳቸው እርስ በርስ መቃቃርን ሲያስከትል እንመለከታለን፡፡

መ. አንዱ የአካል ክፍል ባልተሰጠው የጸጋ ስጦታ ላይ በማተኰር የተሰጠ ውን የጸጋ ስጦታ ቸል ሲልና እንደሚገባ ሳይጠቀምበት ሲቀር፡- «እግር፣ እኔ እጅ አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ብትል፣ ይህን በማለትዋ የአካል ክፍል መሆንዋ ይቀራልን? ጆሮም፣ እኔ ዐይን አይደለሁም ቢል፣ ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? አካል ሁሉ ዐይን ቢሆን መስማት ወዴት በተገኘ? ሁሉም መስማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ? አሁን ግን እግዚአብሔር እንደ ወደደ





ብልቶችን እያንዳንዳቸው በአካል አድርጓል፡፡ ሁሉም አንድ ብልት ቢሆንስ አካል ወዴት በሆነ? ዳሩ ግን አሁን ብልቶች ብዙዎች ናቸው አካል ግን አንድ ነው፤» (1ቆሮ. 12÷15-20)፡፡

ሠ. የራስን የጸጋ ስጦታ ብቻ በመመልከት በሌላው የጸጋ ስጦታ መጠቀም ያለመፈለግ አዝማሚያ ሲታይ ወይም የሌላው የጸጋ ስጦታ ዝቅ ሲደረግ ፡-
«ዐይን እጅን አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን አታስፈልጉኝም ሊላቸው አይችልም፤» (1ቆሮ. 12÷21)፡፡

ረ. ከላይ የኅብረት ማጠናከሪያዎች ተብለው የተጠቀሱት (ትሕትና፣ የውሃነት፣ ትእግሥት፣ ሰላም፣ ፍቅር ሲጓደሉ፡-)

እንግዲህ ኅብረት አስፈላጊ እንደ መሆኑ መጠን በጥንቃቄ መያዝም ስለ አለበት፣ ከጌታ የተሰጠንን የመንፈስ አንድነት ለማሳደግና ለመጠበቅ እንትጋ፡፡

ቃሉ፣ «በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ» (ኤፌ. 4÷3) ይላልና፡፡

__እግዚአብሔር የመንፈስን አንድነት ያብዛልን!__

## ትምህርት አምስት፡- የአማኞች ኅብረት

የመታወቂያ ቁጥር፤ ______________________________
ስም፤ ______________________________
አድራሻ፤ ______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

1. የአማኞች ኅብረት መነሻው (መሠረቱ) ምንድን ነው?
2. በመዝሙረ ዳዊት 132 (133) የአማኞች ኅብረት በምን በምን ተመስሏል? እያንዳንዱ ምንን ያመለክታል?
3. የክርስቲያኖችን ኅብረት ከሌላው ኅብረት ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?
4. አማኞች በኅብረት ሲኖሩና በየጊዜው እየተገናኙ ሲመካከሩ፣ ምን ምን ውጤቶች ይከተላሉ?
5. የክርስቲያኖች ኅብረት የሚሻክረው ወይም የሚናጋው ምን ምን ሲሆን ነው?
6. አማኞች አንድ ሲሆኑ የሚመሰክሩት (የሚያረጋግጡት) ምንድነው?
7. እንደ አንድ አማኝ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ማድረግ ያለብህ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ከእነዚህ መካከል በአንተ ሕይወት፡-
    - በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል የምትለው የትኛው ነው?
    - መሻሻል ያለበት የትኛው ነው?